# የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ

**ዘላቂ የልማት ግብ 4ን ለመምታት በተደራሽነት፣**

**በፍትሃዊነትና በአካታችነት ላይ የሚያተኩር**

(2015-2022 ዓ.ም)

መስከረም 2015 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

## ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | v |
| ምስጋና | vi |
| ክፍል አንድ | 1 |
| አጠቃላይ ገጽታ | 1 |
| 1.1. መግቢያ | 1 |
| 1.2. የስትራቴጂው ክለሳ አስፈላጊነት | 2 |
| 1.3. የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት | 2 |
| 1.4. የመሰረታዊ ቃላት ትርጉም/ ፍቺ | 3 |
| ክፍል ሁለት | 6 |
| የልዩ ፍላጎት ትምህርት ነባራዊ ሁኔታ ትንተና | 6 |
| 2.1. ዳራ | 6 |
| 2.2. የህግ ማዕቀፎች | 7 |
| 2.3. 2004 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ግምገማ | 8 |
| 2.3.1. የ2004ቱ ስትራቴጂ የይዘት ግምገማ | 8 |
| 2.3.2. የ2004ቱ ስትራቴጂ አተገባበር ግምገማ | 10 |
| ክፍል ሦስት | 14 |
| የስትራቴጂው ዓላማና መርሆች | 14 |
| 3.1. አጠቃላይ ዓላማ | 14 |
| 3.2. ዝርዝር ዓላማዎች | 14 |
| 3.3. የስትራቴጂው መርሆች | 15 |
| ክፍል አራት | 16 |
| የስትራቴጂው የትኩረት መስኮች እና የአተገባበር ሂደት | 16 |
| የትኩረት መስክ 1፡- አካታችና ውጤታማ የሆነ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አደረጃጀት፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል። | 16 |
| የትኩረት መስክ 2፡-ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች በፍትሃዊነት፣ በእኩልነትና በውጤታማነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል። | 16 |
| የትኩረት መስክ 3፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂና ሌሎች አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። | 17 |
| የትኩረት መስክ 4፡- የትምህርት ቤቶችን መሰረተ- ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል | 18 |
| የትኩረት መስክ 5፡- በየደረጃው ላሉ መምህራንና አመቻቾች የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል። | 19 |
| የትኩረት መስክ 6፡- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር ይፈታል። | 20 |
| የትኩረት መስክ 7፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተስማሚ ስርዓተ-ትምህርት ይዘጋጃል። | 21 |
| የትኩረት መስክ 8፡- የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ሥርዓትን መዘርጋት | 23 |
| የትኩረት መስክ 9፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን የመለየትና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ይዘረጋል። | 24 |

የትኩረት መስክ 10፡- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ውጤታማ የሚያደርግ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል። ........ 25
የትኩረት መስክ 11፡- ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር ውጤታማ የድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል። ........ 25
የትኩረት መስክ 12፡- የተቀናጀ ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል ........ 26
ክፍል አምስት ........ 28
የስትራቴጂው ተቋማዊ የአፈፃፀም ማዕቀፍ ........ 28
5.1. መግቢያ ........ 28
5.2. የስትራቴጂው አፈፃፀም ሂደት ........ 28

## መቅድም

ትምህርት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣትና ድህነትን ለመቀነስ ዓይነተኛ መሳሪያ ነው። መንግስት ዘላቂ የልማት ግቦችን ለመምታት ቃል ገብቶ በቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን ከእነዚህም ግቦች አንዱና ዋነኛው የትምህርት የልማት ግብ ነው።

ህገ መንግስቱ ዜጎች ትምህርት እንዲያገኙ የሚሰጠውን መብት እና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችና ኮንቬንሽኖች መሰረት በማድረግ ትምህርትና ስልጠና ለሁሉም ዜጎች በተለይም ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና ሰልጣኞች ተደራሽ ለማድረግ የመጀመሪያው የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ በ1998 ዓ.ም የተቀረጸ ሲሆን ይህም ስትራቴጂ ለአምስት ዓመታት ካገለገለ በኋላ በ2004 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲተገበር መቆየቱ ይታወሳል።

የእነዚህ ስትራቴጂዎች ትግበራ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንን በማሰልጠን፣አጫጭር የክህሎት ስልጠናዎችን ለመምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች በመስጠት፣በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን በመስራት እና የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በማስፋፋት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ እንዲጨምር አድርጓል። ይሁን እንጂ ለሁሉም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ህጻናት፣ወጣቶችና ጎልማሶች ትምህርትን ከማዳረስና ልዩ ፍላጎት ትምህርትን እውን ከማድረግ አኳያ አሁንም ብዙ ክፍተቶች ይታያሉ።በየደረጃው ያለው የትምህርት አመራር ስለ ልዩ ፍላጎት ያለው ግንዛቤና ቁርጠኝነት ማነስ፣የመማሪያ አካባቢ ምቹ አለመሆን፣የመምህራን ስልጠናው ተግባር ተኮር አለመሆን፣ደካማ የማስተማር ዘዴዎች፣ብቃት ያለው የምዘና አሰጣጥ አለመኖርና ችግሮችን መለየት አለመቻል በመማር እድል ላይ የተጋረጡ ዋና ዋና እንቅፋቶች ናቸው። በእነዚህም ችግሮች ምክንያት ትምህርት ቤቶችና መምህራን ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች አካቶ ለማስተማር ሲቸገሩ ይስተዋላል።

በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ያለውን ክፍተት ለመቅረፍ አሁን ዓለም አካቶ ትምህርትን በመተግበር የደረሰበትን ደረጃ እና ኢትዮጵያም ከደረሰችበት የእድገት ደረጃ አንጻር በመገምገም ትምህርት ሚኒስቴር ይህን የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ለሁለተኛ ጊዜ በማሻሻል አዘጋጅቷል። የስትራቴጂው ዋና ግብም ከትምህርት ለተገለሉ እና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ጥራት ያለው አካታችና ፍትሃዊ ትምህርትን ተደራሽ ማድረግ ነው።

ስትራቴጂው ከቁልፍ ከባለድርሻ አካላትና ከትምህርት የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ሲሆን ትምህርት ሚኒስቴርም ይህንን ስትራቴጂ በመተግበር የአስር ዓመቱን የትምህርት እቅድና ዘላቂ የትምህርት ልማት ግብን ለማሳካት ወደፊትም ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም የትምህርት የልማት አጋሮች ጋር ሁሉ ተባብሮ የሚሰራ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

ፋንታ ማንደፍሮ (ዶ/ር)

የአጠቃላይ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

# ምስጋና

ይህ የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርት ትግበራ ሀገራዊ ስትራቴጂ ከ2015 እስከ 2022 ዓ.ም እንዲያገለግል በኢ.ፌ.ድ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና በላይት ፎር ዘ ወርልድ ኢንተርናሽናል ትብብር ተዘጋጅቷል። ትምህርት ሚኒስቴር በዚህ ስትራቴጂ ዝግጅት የአርብቶ አደርና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች ላሳዩት ቁርጠኝነትና ሙያዊ ተሳትፎ እውቅና ሊሰጥ ይወዳል።

ላይት ፎር ዘወርልድ ኢንተርናሽናል የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በስትራቴጂው ዝግጅት ወቅት ላደረገው አስተዋጽኦ የላቀ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ከዚህ በተጨማሪ የስትራቴጂውን ረቂቅ በባለድርሻዎች ለማስገምገምና ግብዓት ለማሰባሰብ በተዘጋጀው ሀገራዊ የምክክር አውደ ጥናት ላይ ለተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በሙሉና በምክክር ስብሰባው የተገኙ ሀሳቦችን በክለሳ ለማካተት ባለድርሻ አካላትን ወክለው ከዲቦራ ፋውንዴሽን፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍልና ከኤች ፒ ዲ ኦ (HPDO) የተወከሉ ባለሙያዎች ስትራቴጂው የመጨረሻ ቅርጹን እንዲይዝ ላደረጉት ሙያዊ ድጋፍ ምስጋናችን ይድረሳቸው።

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ ገጽታ

## 1.1. መግቢያ

ትምህርት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት መሰረት ከመሆኑም በላይ ለሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ በትምህርት የለማ የሰው ኃይል በሚኖርበት አካባቢ የሚከሰቱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮችን በብቃት በመሻገር ለማህበረሰቡ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይችላል፡፡ በመሆኑም የትምህርት አገልግሎትን ለዜጎች ሁሉ ያለአድልዖ ማቅረብ ማህበራዊ ጠቀሜታው እጅግ የላቀ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር መንግስት መሰረታዊ ትምህርትን ለዜጎች ሁሉ ለማቅረብ ያለውን ፍላጎትና ቁርጠኝነት በህገ መንግስቱ፣ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው፣ በትምህርት ፍኖተ ካርታውና በሌሎች ሰነዶች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ህጻናት የትምህርት አገልግሎት እንደሚያገኙ አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተቀብሎ አጽድቋል፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ በ1998 ዓ.ም በማዘጋጀት ለተከታታይ አምስት ዓመታት ሲተገበር ቆይቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክርና ግምገማ በማድረግ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ በ2004 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ስትራቴጂዎች ቢዘጋጁም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማግኘት ባለመቻላቸው የትምህርት ተሳትፎአቸውና ውጤታቸው በሚፈለገው መጠን መሻሻል አልቻለም፡፡ በመሆኑም የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በማሻሻል ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ጥራትና ተገቢነቱን የጠበቀ ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥን ውጤታማ ለማድረግ በትግበራ ላይ ያለውን ስትራቴጂ ለሁለተኛ ጊዜ በመከለስ ይህ አገራዊ የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህም ስትራቴጂ አምስት ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍል አንድ አጠቃላይ ገጽታ ሲሆን በውስጡም መግቢያ፣ ፣የስትራቴጂው ክለሳ አስፈላጊነት፣ የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት እና መሰረታዊ የቃላት ትርጉም/ፍቺን ይዟል፡፡ በክፍል ሁለት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ነባራዊ ሁኔታ ትንተና የቀረበ ሲሆን ከአካቶ ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎች፣ዳራና የ2004 ዓ.ም

ሰትራቴጂ ግምገማ ግኝቶችን ይዟል። ክፍል ሶስት የስትራጂው ዓላማና መርሆችን ይዟል። ክፍል አራት የስትራቴጂው የትኩረት መስኮችና አተገባበር ሂደት የያዘ ሲሆን በክፍል አምስት ደግሞ የስትራቴጂው ተቋማዊ የአፈጻጸም ማዕቀፍ ተገልጿል።

## 1.2. የስትራቴጂው ክለሳ አስፈላጊነት

በ1998 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው የልዩ ፍላጎት /የአካቶ ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ በ2004 ዓ.ም ተከልሶ በስራ ላይ ይገኛል። ይህም ስትራቴጂ ተግባራዊ በመሆኑ አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በሚከተሉት ምክንያቶች መከለስ አስፈልጓል።

- በስትራቴጂው ይዘት ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮች በመኖራቸው፣
- በአተገባበር ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና ክፍተቶችን ለመፍታትና ለማስተካል፣
- ትምህርት በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ከአዳዲስና ወቅታዊ አሰራሮችና አስተሳሰቦች ጋር ለማጣጣም፣
- ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ድንጋጌዎችና ኮንቬንሽኖች እንዲሁም ከአሥር ዓመት የትምህርት ልማት ዕቅድና ከስድስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ ነው።

## 1.3. የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

- የተጠቃሚዎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻሉም ባሻገር ለራሳቸው ክብርና ዋጋ የመስጠት ስሜትን ያዳበሩ አምራች ዜጎችን ለማፍራት ስለሚያስችል፤
- ለግለሰቦችም ሆነ ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ስለሚያስገኝ፤
- መድልዎን በማጥፋትና ማህበራዊ ዕኩልነትን በማስፋፋት ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ለመፍጠር አስተዋፅዖ ስለሚያበረክት፤
- የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በማጠናቀቅ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለመምታት ስለሚረዳ፤
- ልዩ ትምህርት ቤቶችን ከማቋቋም ይልቅ አካቶ ትምህርትን መተግበር ወጭ ቆጣቢና አዋጭ በመሆኑ፤

- አካቶ ትምህርት ሁሉም ልጆች በትምህርት ቅስሞሽ (learning) ውስጥ ችሎታቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲያዳብሩና እርስ በእርስ እንዲማማሩ ስለሚረዳ፣
- አካል ጉዳተኛ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ እንዲማሩ ስለሚያስችል፤
- የትምህርት አመራሩ ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ አገልግሎት ለመስጠት ስለሚያስችለው አካቶ ትምህርትን በሁሉም ት/ቤቶች በውጤታማነት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ምንም እንኳን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አካል ጉዳተኞችና የመማር ተግዳሮቶች ያሉባቸው ህፃናትና ወጣቶች በአካቶ ትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድጋፍ እየተደረገላቸው መማር የሚችሉ ቢሆንም፤ ከፍተኛ (Severe) እና ተደራራቢ (Multiple) ጉዳት ያሉባቸውን ልጆች ማለትም፡ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት (Intellectual Disability)፤ ኦቲዝምና ተዛማጅ የእድገት ተግዳሮቶች ያሉባቸውን ልጆች (Autism Spectrum Disorder)፤ መስማትናማየት የተሳናቸውን (Deaf-Blind)፤ ልዩ ተሰጥዎና ችሎታ ያላቸውን ልጆች ለማስተናገድ እንደ አማራጭ በልዩ ትምህርት ቤቶች (special schools) ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ልዩ ክፍሎች (special classes) ውስጥ በልዩ የትምህርት አቅርቦት ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።

## 1.4. የመሰረታዊ ቃላት ትርጉም/ ፍቺ

**ልዩ ተሰጥዎና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች፡** በአእምሮ ምጡቅነት፣ በፈጠራ፣ በተለየ የቀለም ትምህርት ወይም የአመራር ብቃት ወይም በስዕል፣ በቅርፃ ቅርፅ፣ በሙዚቃ፣ በዳንስ፣ በስፖርት እንቅስቃሴ፣ ወዘተ የተለየ ችሎታ እንዳላቸው የሚያሳዩትን ማለት ነው።

**ልዩ ትምህርት ቤት፡-** ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ብቻ የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት ተገቢ በሆነ የሰው ኃይል፣ የትምህርት ቁሳቁሶችና አጋዥ መሳሪያዎች የተደራጀ ትምህርት ቤት ነው።

**ልዩ ክፍል፡-** ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ለማስተማርና ተስማሚ ክሂሎችን ለማሰልጠን የሚያስችል በመደበኛ ት/ቤቶች ውስጥ ተገቢ በሆነ የሰው ኃይል፣ የትምህርት ቁሳቁሶችና አጋዥ መሳሪያዎች የተደራጀ የመማሪያ ክፍል ነው።

**ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፡-** በተለያዩ ምክንያቶች በትምህርታቸው ላይ የመማር ተግዳሮቶች የሚያጋጥማቸው ተማሪዎችን የሚመለከት ሲሆን እነዚህም ተማሪዎች ተጨማሪ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ ድጋፍ የሚሹ ናቸው።

**ልዩ ፍላጎት ትምህርት፡-** ሥርዓተ ትምህርትን፣ የተግባቦት መንገዶችን ወይም የመማር ማስተማር አካባቢን በማስማማት የትምህርት ቅስሞሽ ግለሰባዊ ልዩነትን መሠረት በማድረግ አገልግሎት የሚሰጥ የትምህርት ዓይነት ነው። ይህም ማንኛውንም በልዩ ት/ቤቶች፣ በልዩ ክፍሎች እና በአካቶ ትምህርት የሚሰጡትን የትምህርት አገልግሎችን እና ድጋፎችን ያጠቃልላል።

**ሜይንስትሪሚንግ** /mainstreaming/፡- የትምህርት ዘርፉ የሥራ ክፍሎች በጎናዊና ተዋረዳዊ አደራጀቶች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በፖሊሲ ውስጥ በማካተት፣ በእቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የትግበራ አካል ማድረግን ይመለከታል።

**ተዘዋዋሪ መምህር** የምንለው በልዩ ፍላጎት ትምህርት በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ደረጃ ያለው ሆኖ የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በማቋቋምና በማደራጀት ዙሪያ አጫጭር ስልጠናዎች ወስዶ ለድጋፍ መስጫ ማዕከሉ እና በዙሪያው ላሉ ሳተላይት ት/ቤቶች ማህበረሰብ፣ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች፣ ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ወላጆች እና ለሌሎች የአካባቢው ማህበረሰብ ድጋፍ የሚያደርግና ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ባለሙያ ነው።

**ተደራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው፡-** ከአንድ በላይ የአካል ጉዳት ያላቸውና ከጉዳታቸው ዓይነትና መጠን ጋር በተያያዘ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚያሻቸውን ማለት ነው።

**አካቶ ትምህርት፡-** ልዩ የትምርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፣ በእድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በፆታ፣ በቀለም፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በባህል ልዩነት ወይም በሌሎች ሁኔታዎች መድልዖ ሳይደረግባቸው በመደበኛ ት/ቤቶች የተመቻቸ ትምህርት የሚሰጥበት አቀራረብ ነው።

**ኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር** (autism spectrum disorder) ፡ በማህበራዊ መስተጋብር፣ በንግግር እና በንግግር አልባ ግንኙነት ላይ የሚከሰት ውስንነት እንዲሁም

ተደጋጋሚ ድርጊቶችን የማድረግ ባህርይን የሚያካትት ውስብስብ የሆነ በእድገት ውስጥ የሚታይ ተግዳሮት ነው።

**የመስማትና ማየት ጉዳት** (deaf-blind)፡- ይህ ሁኔታ የሚታየው በግለሰቡ ላይ የደረሰው ጉዳት በሁለቱም የስሜት ህዋሳት ማለትም በመስማትና በማየት ላይ ሲሆን ነው።

**የአዕምሮ እድገት ውስንነት፡-** በማመዛዘን፣ በመረዳትና በማስታወስ፣ ችግር በመፍታት፣ በእለት-ተዕለት የአኗኗር ክሂሎች እና በማህበራዊ መስተጋብር ላይ የሚያጋጥም የዕድገት ዘመን ተግዳሮት ነው።

**የአካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማዕከል፡-** በልዩ ልዩ ቁሳቁሶችና የአካል ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች የተደራጀ እና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለሳተላይት ት/ቤቶች ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎችን ያካተተ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው።

# ክፍል ሁለት

## የልዩ ፍላጎት ትምህርት ነባራዊ ሁኔታ ትንተና

### 2.1. ዳራ

የአካል ጉዳተኞች ትምህርት እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ በልግስና፣ በዕምነት ተቋማት እና በበጎ ፍቃደኞች ድጋፍ እየተደረገላቸው የቀለም ትምህርትና የክሂሎች ስልጠና ሲሰጣቸው እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ልዩ ትምህርት እንደ አንድ የእውቀት ዘርፍ መስራት የጀመረበት ጊዜ ሲሆን ዋናው ተግባሩም መዋቅር በመፍጠር ስራውን በቅንጅት መምራት ነበር። ይህም ስራ የተጀመረው አካል ጉዳተኛ ህፃናትን እንደአካል ጉዳታቸው ዓይነት በመለየት ለማስተማር ይቻል ዘንድ ልዩ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም፣ መምህራንን በማሰልጠንና እና ለትምህርት ስራው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን በማሟላት ነበር።

በኢትዮጵያ ውስጥ ልዩ ትምህርት ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ በ1917 (እ.አ.አ) በሚሲዮናውያን መጀመሩን ሰነዶች ያረጋግጣሉ። በሀገሪቱ ውስጥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አሰጣጥ ከሚሲዮናውያን በተጨማሪ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ባልተቀናጀ መልኩ ሲሰጥ ቆይቷል። ይሁን እንጂ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተደራሽነት አዝጋሚ ነበር። ለአብነትም በ2019/20(2012 ዓ.ም) የመደበኛው ትምህርት ተሳትፎ 104.9 በመቶ ሲሆን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ 11.1 በመቶ ነበር።

ይህንን የትምህርት አገልግሎት በተቀናጀና ስርዓት ባለው መልክ ለማቅረብ፣ ልዩ ፍላጎት ትምህርትን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ በማድረግና የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ እንዲቻል በሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር ውስጥ ተካቷል። ይህንንም መሰረት በማድረግ በ2006 (እ.አ.አ) በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ለአምስት ዓመታት ካገለገለ በኋላ በ2004 ዓ.ም ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ምክክር ተሻሽሎ በስራ ላይ ውሏል። ይህም ስትራቴጂ የአካል ጉዳተኛ ዜጎች "መብትን መሰረት ያደረገ" ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል የሚለውን የአካቶ ትምህርትን መሰረታዊ ፍልስፍናን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነበር።

## 2.2. የህግ ማዕቀፎች

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (እ.አ.አ) 1948 ባወጣው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ በአንቀጽ 26 ትምህርት እንደ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብት የሚቆጠር ሲሆን ለዜጎች ምሉዕ የሰብእና እድገት፣ ለሰው ልጆች መብት እንዲሁም መሰረታዊ ነጻነቶች አክብሮት እንዲኖረው ትምህርት በነጻና አስገዳጅ መንገድ የመስጠትን መርህ ይከተላል።

በ1989 (እ.አ.አ) የወጣው የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 2 በሕጻናት በተለይም በአካል ጉዳተኛ ሕጻናት ላይ መድልኦ እንዳይደረግባቸው ይደነግጋል። ከዚህም በተጨማሪ አንቀጽ 23 አካል ጉዳተኛ ህፃናት "ውጤታማ የሆነ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የጤና አጠባበቅ፣ የተሃድሶ አገልግሎት..."ሊሰጣቸው ይገባል። ይህም የህፃኑ ግለሰባዊ እድገትና ማህበራዊ ውህደት እንዲፋጠን ምቹ ሁኔታን በሚያመቻች መልኩ መሆን ይኖርበታል በማለት ይደነግጋል።

በ2006 (እ.አ.አ) የወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አካል ጉዳተኞች እንደ ሌሎች ሕጻናት ፣ወጣቶችና ጎልማሶች ሁሉ እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም ምንም ዓይነት መድልኦና መገለል ሳይደረግባቸው በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የመሳተፍ መብት እንዳላቸውና የሀገራትም የትምህርት ሥርዓት አካታች መሆን እንዳለበት አጽንኦት ይሰጣል። ይህንን ኮንቬንሽን ኢትዮጵያ በ2010 (እ.አ.አ) በአዋጅ ቁጥር 676/2010 አጽድቃ በመተግበር ላይ ትገኛለች።

በተጨማሪም አገሪቱ ዘላቂ የልማት ግቦችን ለመተግበር ቁርጠኝነት አሳይታለች። ከነዚህም የልማት ግቦች ውስጥ ግብ 4 ትኩረት የሚያደርገው ትምህርት ላይ ሲሆን እሱም "ጥራት ያለው አካታችና ፍትሃዊ ትምህርትን ማረጋገጥና የዕድሜ ልክ የትምህርት ዕድልን ለሁሉም ማስተዋወቅ" እንደሆነ ያሳያል።

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀፅ 3 የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ በመንግስት ሀብት በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት እንዳላቸው የሚገልጽ ሲሆን በተለይም በንኡስ አንቀፅ 5 ደግሞ "መንግስት የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን....ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደ መጠን እንክብካቤ ያደርጋል" በሚል ተደንግጓል።

በ1986 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ የዋለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ትምህርት ያለ አንዳች አድልኦ ለሁሉም ህፃናት እንደሚሰጥና ከትምህርት ልማት ዘርፍ ትኩረት ተነፍገዋቸው ለኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግ ሲያረጋግጥ ልዩ ፍላጎት ትምህርትን በተመለከተም ፖሊሲው፤

- አካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው ትምህርት እንደሚሰጣቸው (ቁጥር 2.2.3)፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርትና ስልጠና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች እንደሚሰጥ (ቁጥር 3.2.9)፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎች በመደበኛው የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም እንደሚሰለጥኑ (ቁጥር 3.4.11) እና
- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጉ የድጋፍ ግብዓቶች እንደሚሟሉ (ቁጥር 3.7.6) ይገልፃል።

በተጨማሪም የ10 ዓመት የትምህርት ልማት እቅዱ (ከ2013 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም) ትኩረት ከሰጠው አንዱና ዋነኛው ጉዳይ አካታች የሆነ የትምህርት ተሳትፎና ውስጣዊ ብቃት ሲሆን ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ መጨረሻ ድረስ ነፃና የግዴታ ትምህርት በማቅረብ የዜጎችን መብት ማክበር እንደሚገባ አመላክቷል።

## 2.3. 2004 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ግምገማ

በዚህ ክፍል ውስጥ የዳሰሳ ጥናት እና የቅኝት ግኝት (Desk Review) በማካሄድ የ2004 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ይዘትና አተገባበር ሂደት በዝርዝር በመገምገም አፈጻጸሙን በጥንካሬና በድክመት ማስቀመጥ ተችሏል።

### 2.3.1. የ2004ቱ ስትራቴጂ የይዘት ግምገማ

በዳሰሳ ጥናቱ፣ በተዛማጅ ጥናትና ቅኝት ግኝት መሰረት በ2004 ዓ.ም በተዘጋጀው ስትራቴጂ ይዘት ላይ የታዩ ጥንካሬዎችና ጉድለቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 2.3.1.1. ጠንካራ ጎኖች

- ሰነዱ የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርትን የወደፊት አቅጣጫ በግልፅ ያመላከተ መሆኑ፣
- የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርትን ለመተግበር የሚያስችሉ ቁልፍ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ማካተቱ፣
- የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ስላላቸው ተማሪዎች ትምህርት ጉዳይ ግንዛቤና ተሳትፎ እንዲኖራቸው እድል መፍጠሩ፣
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዘርፍ የትምህርት አመራሩ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲከናወኑ በስትራቴጂ ሰነዱ ውስጥ በመገለጹ ያለውን የበጀት ችግር ለመቅረፍ GEQIP-E ውስጥ እንዲካተት መደረጉ የሚጠቀሱ ናቸው።

#### 2.3.1.2. ደካማ ጎኖች

- ከትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ስትራቴጂውን ለመተግበር የሚያስችል ተዋረዳዊና ጎናዊ የሥራ ግንኙነትን በግልፅ አለማመላከቱ፤
- የመማር ተግዳሮት ያለባቸውን፣ ልዩ ተሰጥዎና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የመለያ መሳሪያና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት አለመኖሩ፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተስማሚ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አገልግሎት በግልፅ አለመቀመጡ፣
- በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርት ጉዳይ አለመካተቱ፣
- ከፍተኛ የአእምሮ እድገት ውስንነት፣ ኦቲዝም ያለባቸው እና መስማትና ማየት የተሳናቸው (deaf-blind) ሕፃናትና ወጣቶች ትምህርት ጉዳይ አለመካተቱ፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ስለሚሰጠው የኪስ ገንዘብና ሌሎች የማበረታቻ ጥቅማጥቅም ወጥ የሆነ የአፈጻጸም ሂደትና ማዕቀፍ አለማመላከቱ፣
- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን የማበረታቻ ጥቅማጥቅም መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ቢጠቀስም እንዴት እንደሚፈጸም አመላካች የሆነ የአሰራር ስርዓት አለማሳየቱ፣

- ለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ማስፈጸሚያ በጀት መመደብ እንዳለበት ቢገለጽም የአመዳደብ መመሪያና ወጥ የሆነ የበጀት ድልድል ሥርዓት የሚያሳይ አለመሆኑ፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የሽግግር ፕሮፋይል አለመዘጋጀቱ፣
- ሰነዱ የስትራቴጂውን የአተገባበር ውጤቶች(outcome) አለማመላከቱ ተጠቃሾች ናቸው።

## 2.3.2.የ2004ቱ ስትራቴጂ አተገባበር ግምገማ

### 2.3.2.1. ጠንካራ ጎኖች

- በአገሪቱ የሚገኙ ጥቂት ዩኒቨርሲቲዎች በልዩ ፍላጎት/በአካቶ ትምህርት መስክ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም በፒችዲ ደረጃ ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛሉ።
- ከግማሽ በላይ በሚሆኑ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በልዩ ፍላጎት ትምህርት በዲፕሎማ ደረጃ ሥልጠና በመሰጠት ላይ ይገኛል።
- በአገሪቱ በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ተቋማት የአካቶ ትምህርት የማስተዋወቂያ የሥልጠና ማኑዋልና ለተግባር ልምምድ የሚያገለግሉ ሞጁሎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል።
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልሳን የትምህርት ክፍል የሚሰጠው የምልክት ቋንቋ ሥልጠና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ለማሰልጠን ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተሳትፎ ለማሳደግ 874 የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላት ተቋቁመዋል።
- አዲስ የተቋቋሙ የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ለማጠናከር ለማዕከላቱ ርዕሰ መምህራን፣ ለተዘዋዋሪ መምህራን፣ ለወረዳና ለዞን የትምህርት አመራር አካላት፣ ለክልል ትምህርት ቢሮዎች የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል።
- ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍሎች ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የምልክት ቋንቋ መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል።
- በትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምህርት ስታትስቲክስ መሠረት በ2003 ዓ.ም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተሳትፎ 55492

(ወ=32072፣ ሴ=23420) ሲሆን አፈጻጸሙም 3.2 በመቶ ነበር። የእነዚህ ተማሪዎች ተሳትፎ በ2012 ዓ.ም ወደ 323748 (ወ=181942፣ ሴ=141806) ያደገ ሲሆን አፈጻጸሙም 11.1 በመቶ ነው።

- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳይ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ውስጥ በመካተቱ በ2012 ዓ.ም 10236 (ወ=6251፣ ሴ=3985) /0.9 በመቶ/ የሚሆኑ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ።

## 2.3.2.2. ደካማ ጎኖች

- ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ወረዳ ት/ጽ/ቤት ድረስ የአካቶ ትምህርትን ለመምራትና ለመተግበር የሚያስችል ወጥ የሆነ አደረጃጀት አለመኖሩ፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን ወይም ተዘዋዋሪ መምህራን የደረጃ እድገት መሰላል፣ የስራ መደባቸውንና ስምሪታቸውን በግልጽ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣
- የተጠያቂነት አሰራር ስርዓት ያለመኖር ልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ውጤታማ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣
- በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ላይ የሚገኙ አስፈጻሚና ፈጻሚዎች የስትራቴጂውን ውጤታማ አተገባበር ለማሳለጥ የነበራቸው ቁርጠኝነትና ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮችን በዕቅድ፣ በበጀት፣ በክትትል፣ በግምገማና በሪፖርት ውስጥ አለማካተቱ፣
- በሁሉም የትምህርት እርከኖች ከፍተኛ የሆነ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች እጥረት ከመኖሩ ባሻገር በመምህራን ትምህርት ተቋማት በመሰጠት ላይ ያሉት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ኮርሶች ንድፈ ሃሳብ (theory oriented) ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ምሩቃኑ የተግባር ክሂሎች ውስንነት የሚታይባቸው መሆኑ፣
- በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ውስን በመሆኑ በባለድርሻዎችና በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የተዛባ አመለካከት በስፋት መስተዋሉ፣
- አንዳንድ ክልሎች ለልዩ ፍላጎት ትምህርት መጠነኛ በጀት ቢመድቡም ሌሎች ክልሎች ግን በጀት የማይመድቡ በመሆኑ በስትራቴጂው ትግበራ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣
- ግልፅና አግባብነት ያላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ባለመኖሩና በመረጃ ሰብሳቢዎች ክህሎት ማነስና ቸልተኝነት ምክንያት ተዓማኒ መረጃ ማግኘት አለመቻሉ፣

- ከፍተኛ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት፣ ኦቲዝምና ተዛማጅ የእድገት ተግዳሮቶች ያሉባቸው፣ መስማትናማየት የተሳናቸው (deaf-blind) እና ሌሎች ጉዳቶች ያሉባቸው ዜጎች አገልግሎቱን አለማግኘታቸው፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት የሚያገኙት አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው፤ ዕድሉን አግኝተው በመማር ላይ የሚገኙትም ቢሆኑ ለሚያጋጥሟቸው የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮች በቂ ድጋፍ አለማግኘታቸው፣
- የትምህርት ቤቶች ምድር-ግቢና አገልግሎት አሰጣጥ (መፀዳጃ ቤት፤ ቤተ መፃህፍት፤ የግቢ ውስጥ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰሌዳ፤ መዝናኛ ስፍራ፤ የስፖርት ማዘውተሪያና መጫወቻ ቦታዎች፣ ተዳፋታዊ መተላለፊያ (ramp)፤ ውሃ መጠጫ ቦታ፤ ወዘተ) ለአካል ጉዳተኛ ዜጎች ተደራሽ አለመሆናቸው፣
- የትምህር ቤቶች የሕንፃ ግንባታ ዲዛይን አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አለመሆኑ፣
- የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመሟላታቸው፣
- የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችና አጋዥ የቴክኖሎጂ አቅርቦት አለመሟላት፣
- በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፤ በመምህራን ትምህርት ተቋማት የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች እጥረት በመኖሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት ባግባቡ አለማግኘታቸው፣
- የስርዓተ-ትምህርቱ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች፣ የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የምዘና ስርዓት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች እንደ ፍላጎታቸውና ችሎታቸው ተስማሚ አድርጎ አለመተግበር፣
- አካልጉዳተኛ ጎልማሶች ለትምህርት አገልግሎት ተደራሽ አለመሆናቸው፣
- አወንታዊ ድጋፍ አሰጣጡ ሁሉንም የአካል ጉዳተኞች አለማካተቱ፣
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለታቀፉ የአእምሮ እድገት ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች የሙያ ሥልጠና ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

- በልዩ ትምህርት ቤቶችና ልዩ ክፍሎች የሚያስተምሩ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን ስራው ከሚጠይቀው ጥረት፣ ውስብስብና ክብደት አንጻር የማበረታቻ ጥቅማጥቅም አለመኖሩ፣
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የትምህርት ተደራሽነት፣ተሳትፎና የትምህርት ማጠናቀቅ ለማበረታታት የድጎማ ጥቅማጥቅም አለመኖሩ፣
- ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተገቢውን ግብረ-መልስ መስጠት አለመቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣

## ክፍል ሦስት

## የስትራቴጂው ዓላማና መርሆች

### 3.1. አጠቃላይ ዓላማ

ጥራትና ተገቢነቱን የጠበቀ አካታች ትምህርትና ስልጠና በፍትሃዊነት ተደራሽ በማድረግ የትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚነት መብት ለሁሉም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ለማረጋገጥ።

### 3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በየደረጃው ውጤታማ የሆነ የአካቶ ትምህርት አደረጃጀት በመዘርጋትና የትምህርት አመራርና አስተዳዳርን በማጠናከር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣
- ምቹ የትምህርት ቤት ሁኔታን በመፍጠር፣ የማህበረሰብ ንቅናቄ ስራ በማከናወንና በህብረተሰቡ ውስጥ አካታች ባህልን በመፍጠር ትምህርትና ስልጠናን ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ፣
- ለትምህርት አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ መምህራንና ማህበረሰብ በአካቶ ትምህርት ላይ ግንዛቤና አቅም በማጎልበት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና በፍትሀዊነት እንዲያገኙ ለማስቻል፣
- የመምህራን ትምህርት ተቋማት የሚሰጡትን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስልጠና ፕሮግራም ለማጠናከር፣
- ስርዓተ-ትምህርቱን እንደየተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታ በማስማማት ትምህርትን በፍትሀዊነት ተደራሽ ለማድረግ፣
- የመለያ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት የአካል ጉዳት ልየታና የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓትን በማጠናከር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ አቅም ለመፍጠር፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች መረጃ አያያዝ ስርዓትን ተአማኒነት በማጠናከር ውጤታማ የድጋፍ ስርዓትን ለመዘርጋት፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የትምህርትና ስልጠና መብትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የሀብት ማፈላለግ፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ስርዓትን ለማሻሻል፣

- የባለድርሻ አካላትን ትብብርና ተሳትፎ በማሳደግ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚያስችል የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ስርዓትን ለመገንባት ነው።

## 3.3. የስትራቴጂው መርሆች

- ✓ ትምህርትና ስልጠና ለሁሉም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ መሆን ያለበት ሰብዓዊ መብት በመሆኑ **የመማር መብትን** ማረጋገጥ፣
- ✓ የትምህርት ቤት አገልግሎት መስጫዎች (school facilities) ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት ቅስሞሽ አገልግሎት **ተደራሽ** መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ✓ ለሁሉም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ በመስጠት ትምህርትና ስልጠና **ፍትሃዊ** እንዲሆን ማድረግ፣
- ✓ የትምህርትና ስልጠና ስርዓት እና አገልግሎት በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በስርዓተ ጾታ፣ በኃይማኖት፣ በአካል ጉዳት፣ በቋንቋ ወ.ዘ.ተ ልዩነት ሳይፈጠር ሁሉንም ዜጎች በጋራ እንደፍላጎታቸውና ችሎታቸው በሚያስተናግድ መልኩ **አካታች** ማድረግ፣
- ✓ አካታች የትምህርት ስርዓትን ለማስፈን የባለድርሻ አካላትና የትምህርት ልማት አጋሮች **የጋራ ኃላፊነት** እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ✓ በየደረጃው በሚገኙ መዋቅሮችና በስራ ክፍሎች በሚከናወኑ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ፣ የመመሪያ፣ የፕሮግራም፣ የዕቅድ፣ የክትትልና ድጋፍ ተግባራት የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት እንደ ዋና የስራ አካል ማካተት እና **ሜይንስትሪሚንግ**/Mainstreaming/ ማድረግ፣

## ክፍል አራት

## የስትራቴጂው የትኩረት መስኮች እና የአተገባበር ሂደት

## የትኩረት መስክ 1፡- አካታችና ውጤታማ የሆነ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አደረጃጀት፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል።

**ግብ፡-** የልዩ ፍላጎት/የአካቶ ትምህርት አተገባበርን በየደረጃው በውጤታማ፣ በኃላፊነትና በተጠያቂነት ሊወጣ የሚችል መዋቅርና የትምህርት አመራርና አስተዳደር ዕውን ማድረግ

### ስትራቴጂዎች

- የስራ ሂደት ጥናት በማድረግ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን የሚመራ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ አደረጃጀት ማቋቋም፣
- በየደረጃው ለሚመደቡ ባለሙያዎች የሚያገለግል የስራ ምዘናና የደረጃ ምደባ አወሳሰን ጥናት ማከናወንና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በየደረጃው ለተመደቡ የስራ ክፍሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ተከታታይ የሆነ የሙያ ማሻሻያ የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፣
- በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ ክፍሎች የሚማሩ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ለሚያስተምሩና ለሚደግፉ መምህራንና ርዕሰ መምህራን ልዩ የማበረታቻ ጥቅማጥቅም (Incentive) የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይገለጻል።

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** ከፌዴራል እስከ ወረዳ በየደረጃው የአካቶ ትምህርት ስርዓትን ሊመራ የሚችል በኃላፊነትና በተጠያቂነት አግባብ የተቋቋመ አደረጃጀት ተፈጥሯል።

## የትኩረት መስክ 2፡-ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች በፍትሃዊነት፣ በእኩልነትና በውጤታማነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

**ግብ፡-** ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ

### ስትራቴጂዎች

- ተከታታይነት ያለው የህዝብ ንቅናቄ ስራ መስራት፣
- የትምህርት ቤቶችን አካባቢና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ ማድረግ፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ቅበላና ተሳትፎን የሚያሳልጥ በየደረጃው የትወራ (Projection) እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ካላቸው ዜጎች ወላጆችና አሳዳጊዎች ጋር በቅርበትና በትብብር መስራት፣
- ከጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎችና ከመሰረተ-ማህበረሰብ ተሃድሶ ሰራተኞች (Community Based Rehabiletation) ጋር በመተባበር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ የቤት ለቤት ምዝገባና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት፣
- በልዩ ትምህርት ቤቶች፣ በልዩ ክፍሎች፣ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ የተለየ ትኩረት የሚሹ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያጋጥማቸውን እንቅፋቶች ተቋቁመው በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል የድጎማና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይገለጻል፣
- የመገናኛ ብዙሃንና ሶሻል ሚዲያን በመጠቀም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ስላላቸው ዜጎች ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ የትምህርት ተሳትፎአቸውን ማሳደግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** በሁሉም የትምህርት እርከኖች ልዩ ትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ተሳትፎ ጨምሯል።

### የትኩረት መስክ 3፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂና ሌሎች አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

ግብ፡ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂና ሌሎች አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ

## ስትራቴጂዎች

- ተስማሚ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በአገሪቱ ህግ መሰረት ከቀረጥ ነጻ በሆነ አግባብ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣
- ተስማሚ የትምህርት ቁሳቁሶችንና አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ለማምረት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትብብር መስራት፣
- በመደበኛ ትምህርት ውስጥ የሚሰጥን አይ.ቲ(IT) ትምህርት አካታች እንዲሆን ማድረግ፣
- በቅድመ- አንደኛና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደ ጉዳታቸው ዓይነት በምልክት ቋንቋ፣ በብሬል መጻፍና ማንበብ፣ በዳሰሳ ምልክት ቋንቋ እና በመሳሰሉት ስልጠናዎች መስጠት፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን በምልክት ቋንቋ፣ በብሬል፣ በዳሰሳ ምልክት ቋንቋ እና በሌሎችም ክሂሎች ላይ በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በአካታች የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ተሳትፎን ለማሳደግ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎችን መመደብ፤ ለዚህም የስራ ምዘናና ደረጃ ምደባ አወሳሰን ጥናት በማድረግ አስፈላጊውን ምደባ መስጠት፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** በትምህርቱ ዘርፍ ተሳታፊ የሆኑ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ የዕለት ተዕለት ክሂሎችና ሙያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚነትና የመረጃ ተደራሽነት ውጤታማ ሆኗል።

## የትኩረት መስክ 4፡- የትምህርት ቤቶችን መሰረተ- ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል

ግብ፡ ትምህርት ቤቶችን ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የትምህርት ተሳትፎ ምቹና አካታች ማድረግ

**ስትራቴጂዎች**

- አካታች የትምህርት ቤት ዲዛይን ማዘጋጀትና ተግባራዊ እንዲሆን መስራት፣
- ነባር የትምህርት ቤት ህንጻዎች ሁለንተናዊ ንድፍ (Universal Design) መርሆች መሰረት ተመጣጣኝ ምቹነት (Reasonable Accommodation) እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በትምህርት ቤቶች ስታንዳርድ መሰረት የትምህርት ቤቶች ምድረ-ግቢና አገልግሎት መስጫዎች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ምቹ ማድረግ፤ ለአፈጻጸሙም የተደራሽነት ስታንዳርድ መመሪያ ማዘጋጀት፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** የትምህርት ቤቶች ምድረ-ግቢና አገልግሎት መስጫዎች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተደራሽ ሆነዋል።

**የትኩረት መስክ 5፡- በየደረጃው ላሉ መምህራንና አመቻቾች የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል።**

**ግብ፡-** የአካቶ ትምህርትን በውጤታማነት ሊፈጽምና ሊያስፈጽም የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል መገንባት፣

**ስትራቴጂዎች**

- በቅድመ-ስራ ስልጠና ፕሮግራም ከቅድመ-አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ለሚያስተምሩ መደበኛ መምህራንና ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎች ለሙያው ብቁ የሚያደርግ የተሟሉ ኮርሶች እንዲወስዱና በይዘታቸውም የበለጠ ተግባር-ተኮር እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በየደረጃው በስራ ላይ ለሚገኙ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት መምህራን፣ ባለሙያዎችና ተዘዋዋሪ መምህራን በተግባር ትምህርትና ልዩ ትኩረት ለሚሹ ከፍተኛ እና ተደራራቢ ጉዳት ላለባቸው ዜጎች በቂ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ስልጠና (Upgrading) እንዲያገኙ ማድረግ፣
- የመምህራን ትምህርት ተቋማት አሰልጣኝ መምህራን በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም (Higher Diploma Programme) የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳይን የስልጠናቸው አካል እንዲሆን ማድረግ፣

- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ በአገር ውስጥና በውጪ አገር የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው የትምህርት ተቋማት ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት፣
- ልዩ ተሰጥዎና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተማር የሚችሉ መምህራንን መመልመልና ማሰልጠን፣
- ልዩ ተሰጥዎና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችል መምህራን በስርዓተ-ትምህርት ማበልጸግ ክህሎትና የተፋጠነ ትምህርት ስልት ላይ ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤ ለዚህም የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ፣
- የመደበኛው ትምህርት መምህራን፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና የጎልማሶችና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመቻቾች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች ውጤታማ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተለያዩ አጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ማድረግ።

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** በየደረጃው ያሉ መደበኛና የልዩ ፍላጎት መምህራን፣ የጎልማሶችና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመቻቾች በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ ያላቸው ክሂሎች እና የማስፈፀም አቅም ተገንብቷል።

## የትኩረት መስክ 6፡- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር ይፈታል።

**ግብ፡** በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር ስራዎች በመፍታት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን የትምህርት ተጠቃሚነት ውጤታማ ማድረግ።

### ስትራቴጂዎች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋማት (ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች) ጋር ትስስር በመፍጠር በአካቶ ትምህርት አፈጻጸም ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና እድሎች እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፣

- በመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ስርዓተ-ትምህርት ላይ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የወቅቱን ፍላጎት ሊመልስ በሚችልና የትምህርቱን ጥራት በሚያስጠብቅ ደረጃ ማሻሻያ ማድረግ፣
- በየእርከኑ የሚገኙ መምህራንና የመምህራን አሰልጣኞች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችንና ሰልጣኞችን በሚያስተምሩበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር (Action Research) በማካሄድ ችግሮችን ይፈቱ ዘንድ በስልጠና መደገፍ፣
- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የፖሊሲ ሀሳብ ማመንጨት፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትምህርት ልማት አጋሮችና የአካል ጉዳተኛ ማህበራት በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ውጤታማነት ላይ ጥናት ሲያደርጉ በትብብር መስራት፣
- የጥናት ግኝቶች ወደ ተግባራዊ ፕሮጀክት እንዲቀየሩ ማድረግ።

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** በአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በጥናትና ምርምር ተለይተው መፍትሄ አግኝተዋል።

## የትኩረት መስክ 7፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ተስማሚ ስርዓተ-ትምህርት ይዘጋጃል።

**ግብ፡-** ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የትምህርትና ስልጠና ውጤት ለማሻሻል ስርዓተ-ትምህርቱን አካታች በማድረግ በእውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በስነ-ምግባራቸው ብቁ ማድረግ።

### ስትራቴጂዎች

- በአካቶ ትምህርት ለሚማሩ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የስርዓተ-ትምህርቱ አካል የሆኑትን የትምህርት ግቦች፣ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች፣ የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የምዘና ስርዓት እንደ ፍላጎታቸውና ችሎታቸው ተስማሚ በማድረግ መተግበር፣

- ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ካለባቸው ጉዳት አንጻር በቀለም ትምህርት መዝለቅ ለማይችሉት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (የመንግስትና የግል) የሙያ ስልጠና መርሃ-ግብር ማመቻቸት፤ ዝርዝር ጉዳዩም ይህን ስትራቴጂ ለማስፈጸም በሚዘጋጀው መመሪያ ውስጥ ይገለጻል።
- የፈተና እና ምዘና ስርዓቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች እንደ ጉዳታቸውና የትምህርት ፍላጎታቸው አይነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተስማሚና የተለየ የፈተና እና ምዘና (አዎንታዊ ድጋፍን ጨምሮ) ስርዓት መዘርጋት፤ ለዚህም የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ይውላል።
- የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር የሚያስፈልጋቸውን ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን በመለየት የነፍስ-ወከፍ የትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፤ የመደበኛ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አካታች እንዲሆን ማድረግ፣
- መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር በትምህርት ስርዓቱ የተዘጋጁ የተማሪዎች መማሪያ መጻህፍትን ወደ ዳሰሳ፤ ተደማጭና ለእይታ በሚመች መልክ የሚቀይርና እንደየጉዳታቸው ዓይነት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚሰራጭ የትምህርት ቁሳቁስ የሚያዘጋጅ አገራዊ ማዕከል ማቋቋም፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ህጻናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች ከቤተሰብ ወደ ትምህርት ቤት፣ ከክፍል ወደ ክፍል፣ ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም እንዲሁም ከትምህርትና ስልጠና ሂደት ወደ ስራ መስክ በሚሸጋገሩበት ወቅት በፊት በነበሩበት ቦታ ይደረግላቸው የነበረውን ድጋፍና አጠቃላይ የባህሪ ገጽታ (Profile) የሚገልጽ ማስረጃ በማዘጋጀት የትስስር ስርዓት መዘርጋት፤ ዝርዝር ጉዳዩም ይህን ስትራቴጂ ለማስፈጸም በሚዘጋጀው መመሪያ ውስጥ ይገለጻል።

**የሚጠበቅ ውጤት፦** ስርዓተ-ትምህርቱ አካታች በመሆኑ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የትምህርት ተሳትፎ፣ መጠነ ሽግግር፣ የመዝለቅ ምጣኔና የማጠናቀቅ ምጣኔ ውጤታማ ሆኗል።

### የትኩረት መስክ 8፡- የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ሥርዓትን መዘርጋት

ግብ፡- የአካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማእከላትን በማስፋፋት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላትና በማደራጀት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ውጤታማ ድጋፍና የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን ማሻሻል

### ስትራቴጂዎች

- የአተገባበር መመሪያ በማዘጋጀት በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ የመለያ፣ የዳሰሳ ማዕከላት በማቋቋም እና የሪፈራል ስርዓት በመዘርጋት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች የተደራጁ ማዕከላትን በየክልሉ/ከተማ አስተዳደር በማቋቋም የምልክት ቋንቋ፣ የብሬይል መጻፍና ማንበብ እንዲሁም በልዩ ልዩ ሙያዎች ለመምህራን ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በትግበራ ላይ ያለውን የክላስተር ትምህርት ቤቶችን ወደ አካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከልነት የመለወጥ ሂደት በማስፋት በክልል/ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች፣ በዞን ትምህርት መምሪያዎች እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች አማካኝነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፤ ይህም የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ለማቋቋምና ለመምራት በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል።
- የአካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን የአተገባበርና የአፈፃፀም ሂደት በጥናትና ምርምር በየጊዜው በመፈተሽ የማሻሻያ እርምጃዎችን መውሰድ፣
- የጉድኝት ማዕከላት ትምህርት ቤቶችን በሰለጠነ የሰው ሀይል እና መሰረታዊ የሆኑ ተስማሚ የትምህርት ቁሳቁሶችና ቴክኖሎጂዎች (ብሬይል ወረቀት ስሌትና ስታይለስ፣ ተናጋሪ የሂሳብ ማሽን፣ አባከስ፣ ብሬል ታይፕ ራይተር፣ ተናጋሪ መጻህፍት(Talking Books)፣ ዲጅታል መቅረፀ-ድምፅ፣ ተናጋሪ ሶፍትዌሮች የተጫኑ ኮምፒውተሮች፣ የምልክት ቋንቋ መጻህፍት፣ የብሬይል መጻህፍት፣ የጎላ ጽሁፍ፣ የጽሁፍ ማጉያ መሳሪያዎች፣ አማራጭና አጋዥ የተግባቦት ዘዴዎችንና ሌሎች) በማሟላት በማዕከላቱ እና በሳተላይት ትምህርት ቤቶች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** የአካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ብዛት፣ አደረጃጀትና አገልግሎት አሰጣጥ ተሻሽሏል።

**የትኩረት መስክ 9፡- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን የመለየትና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ይዘረጋል።**

**ግብ፡-** ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን የመለየትና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ማሻሻል።

**ስትራቴጂዎች**

- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የልየታ፣ የመረጃ አያያዝና ድጋፍ አሰጣጥ ስራ ሊመራ የሚችል ቡድን በትምህርት ቤት ደረጃ በማቋቋም ተግባራዊ ማድረግ፤ አጠቃላይ የቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት በመመሪያ ይገጻል።
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በትምህርት ስራ አመራርና መረጃ አቅርቦት (EMIS) ውስጥ በማካተት ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ውጤት አመላካቾች ተተንትነው እንዲዘጋጁ ማድረግ፣
- የቅድመ- አንደኛ እና የአንደኛ ደረጃ የመለያና የድጋፍ አሰጣጥ ማኑዋል እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በማስማማት በሁሉም ትምህርት ቤቶች (የመንግስትና የግል) ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸውና ፍላጎት ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ዕድሜቸው ለትምህርት የደረሱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች ብዛት (Prevalence) ላይ አገራዊ ጥናት ማድረግ፣
- ልዩ ተሰጥዎ እና ችሎታ ያላቸውን ህፃናትና ወጣቶች ለመለየት የሚያስችል የመለያና ዳሰሳ መሳሪያ (IQ Test, Aptitude Test and Achievement Test) በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጅበትና ተግባራዊ የሚደረግበት ማዕከል ማቋቋም፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይገለጻል።

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** ወቅቱን የዋጀ የመረጃ ስርዓት ተዘርግቶ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱና በትምህርት ላይ የሚገኙ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎችን በአካል ጉዳታቸውና በልዩ የትምህርት ፍላጎታቸው ተለይተው በየደረጃው መረጃ ተጠናክሯል፤ ለዕቅድ ዝግጅትና ውሳኔ አሰጣጥም ዝግጁ ሆኗል።

## የትኩረት መስክ 10፡- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ውጤታማ የሚያደርግ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል።

**ግብ፡-** ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የትምህርት ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚያስችል የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም ስርዓትን ማሻሻል

### ስትራቴጂዎች

- ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከባለሀብቶች፣ ከህብረተሰቡ እና ከሌሎችም አካላት የሀብት ማፈላለግ ስራ መስራት፣
- ከፌደራል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ባሉት ተቋማት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ለመማር-ማስተማርና ድጋፍ አሰጣጥ የሚውል በቂ በጀት እንዲመደብ ማድረግ፣
- የሚመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በመከታተል ተጠያቂነትን ማስፈንና የማሻሻያ ስራ ማከናወን። የበጀት አመዳደቡና ድልድሉን በሚመለከት በአተገባበር መመሪያ ይገለጻል።

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** የአካቶ ትምህርትን ውጤታማ የሚያደርግ በቂ በጀት ተመድቧል፤ የተመደበው በጀትም ለታለመለት አላማ ውሏል።

## የትኩረት መስክ 11፡- ከባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር ውጤታማ የድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል።

**ግብ፡-** የባለድርሻ አካላትን ትብብርና የቅንጅት ስራ በማጠናከር ለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት የሚያደርጉትን ድጋፍና አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማሳደግ።

### ስትራቴጂዎች

- የአካቶ ትምህርትን ለመደገፍና ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትምህርት ልማት አጋሮች፣ የአካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበራትና ሌሎች የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ከግል የትምህርት ተቋማት ጋር

የተጠናከረ ትስስር በመፍጠር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የተቀናጀ ድጋፍ እንዲደረግ የትብብር ማዕቀፍ(MoU) ማዘጋጀትና መተግበር፤ የተቋማቱ ተግባርና ኃላፊነትም በስትራቴጂው የአፈጻጸም መመሪያ ይገለጻል።

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላትና የትምህርት ልማት አጋሮች ጋር የሚከናወኑ ተግባራት ከእቅድ ዝግጅት እስከ ትግበራ ድረስ ያለውን ሂደት በጋራ እየገመገሙ ማሻሻል፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** በአካቶ ትምህርት ላይ ሚና ያላቸው ቁልፍ የባለድርሻ አካላትና የትምህርት ልማት አጋሮች ጋር የትብብር ስራ ተጠናክሯል።

**የትኩረት መስክ 12፡- የተቀናጀ ክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል**

**ግብ፡-** ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው የተቀናጀ የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት በማጠናከር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች የትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚነትና ሁለንተናዊ ድጋፍ አሰጣጥን ማረጋገጥ

**ስትራቴጂዎች**

- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ በወረዳ፣ በክልል/በከተማ አስተዳደር እና በአገር አቀፍ ደረጃ በዓመት ሁለት ጊዜ የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አፈጻጸምን በመገምገም የማሻሻያ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣
- በትምህርት ቤት፣ በወረዳ፤ በክልል/በከተማ አስተዳደር በሚደረጉ የትምህርት ኮንፈረንሶች የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት እንደ አንድ አጀንዳ ተይዞ ለውይይት እንዲቀርብ ማድረግ፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው ዓመታዊ የትምህርት ጉባኤም የአካቶ ትምህርት ትግበራ ትኩረት እንዲሰጠውና በአጀንዳነት ተይዞ ውይይት እንዲደረግበት ማመቻቸት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ኮንፈረንስ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ በማዘጋጀት በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲከበር ማድረግ፤ በኮንፍረንሱ የቀረቡ ጥናትና

ምርምሮች እንዲሁም ተሞክሮች በህትመት ተሰንደው ለንባብና ለመረጃ ምንጭነት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቷል።

# ክፍል አምስት

# የስትራቴጂው ተቋማዊ የአፈፃፀም ማዕቀፍ

## 5.1. መግቢያ

ለዚህ ስትራቴጂ ሁለንተናዊና ውጤታማ ተግባራት የሚመለከተው የዘርፉ ተቋማትና (Multi-Sectoral) የሙያ ስብጥሮች (Interdisciplinary Professions) ተሳትፎና አስተዋፅዖ በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል። ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር የባለድርሻ አካላት፣ ከትምህርት የልማት አጋሮችና ማህበራት ጋር በትብብር ይሰራል። በተለይም በትምህርት ሴክተሩ የታቀፉና በየደረጃው ያሉ የትምህርት ተቋማት እና ውሳኔ ሰጪ የአስተዳደር አካላት የጎንዮሽና በተዋረድ በሚኖራቸው የስራ ግንኙነት ከፌዴራል እስከ ወረዳ ባሉት መዋቅሮች የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን በኃላፊነትና በተጠያቂነት ሊመራ የሚችል የስራ ሂደት በትምህርት ሚኒስቴር እና በክልል/ከተማ አስተዳደር ደረጃ በዴስክ፣ በዞን/ክፍለ-ከተማ እና በወረዳ ደረጃ በቡድን ደረጃ እንዲቋቋሙ ይደረጋል።

## 5.2. የስትራቴጂው አፈፃፀም ሂደት

የዚህ ስትራቴጂ አፈፃፀም ሂደት የአከባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ሲሆን በሚከተሉት ዋና ዋና ዘርፎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። እነርሱም የአመራርና አስተዳደር፣ የትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር፣ የጥራት ማረጋገጥ፣ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ናቸው። የአጠቃላይ የስትራቴጂውን አፈፃፀም የሚመለከት መመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት የሚወጣ ሲሆን ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ወረዳ የሚዋቀሩት የአካቶ ትምህርት ትግበራ የስራ ክፍሎች በየደረጃቸው የሚከተሉት የጋራ ኃላፊነትና ተግባራት ይኖራቸዋል።

- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ፣ በትምህርት ተሳትፏቸው ውጤታማ እንዲሆኑ፣ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አተገባበር ጥራትና ተገቢነት እንዲረጋገጥ በትጋት ይሰራሉ፣
- በሁሉም የትምህርት ሴክተሮች የአካቶ ትምህርት መርሆችና ትግበራዎች በተገቢው መንገድ መካተታቸውን ያረጋግጣሉ፣
- በስትራቴጂው ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አፈፃፀም ሂደትን ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ፣ ይከታተላሉ፣ በመጨረሻም ይገመግማሉ፣

- ለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ማስፈፀሚያ በጀት ማስመደብ፤ ከሌሎች የትምህርት ልማት አጋሮች ተጨማሪ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ድጋፎችን ያፈላልጋል፣
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጥራት እንዲረጋገጥ መከታተል፤ ለዚህም የጥራት መለኪያ ስታንዳርድ አዘጋጅቶ ስራ ላይ ማዋል።

የአካቶ ትምህርት አፈፃፀምን፣ ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረጉ ስራዎችን ከማስተዳደር እና ከማስተባበር ጎን ለጎን ትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉትን ዋና ዋና ስራዎች ተግባራዊ ያደርጋል።

- በዚህ ስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ መመሪያ ለሚያስፈልጋቸው ዝርዝር ጉዳዮች ማስፈጸሚያ መመሪያ ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- ብሔራዊ ስቲሪንግ ኮሚቴ እና የተለያዩ ባለሙያዎችን ያካተተ የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም፣ የኮሚቴዎቹ ተግባርና ኃላፊነት በማስፈጸሚያ መመሪያው ይገለጻል፣
- በክልል/ከተማ አስተዳደር፣ በዞን/ክፍለ-ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ትግበራ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የዚህ ስትራቴጂ የአፈጻጸም ሂደትም መሰረታዊ ጽንሰ-ሃሳቦችን ሳይለቅ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ከኑሮ ዘይቤያቸው ጋር በማስማማት እንዲሁም በሌሎች ክልሎች የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ተግባራዊ ይደረጋል።

በመጨረሻም ይህ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ባሉ የትምህርት ተቋማት ለስምንት (8) ዓመት የሚያገለግል ሲሆን የአተገባበር አፈጻጸሙ ተገምግሞ የሚከለስ ይሆናል።